# እንደተናገረ ተነሥቷል

እንደተናገረ ተነሥቷል

ከገ/ጊዮርጊስ

ይህንን ቃል የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ፤ የመቃብሩን ድንጋይ ሊፈንቅል ከሰማይ የወረደው መልአክ ነው። (ማቴ.፳፰÷፮) በዚህም መድኃኔዓለም ክርስቶስ የተነሣው መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በኀቱም መቃብር መሆኑን እንረዳለን። የጌታን ትንሣኤ ራሱ ባለቤቱ ብቻ የገለጠው አልነበረም ነቢያትም ከዘመናት በፊት በትንቢት መነጽርነት ተመልክተውታል እንጂ። "እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ" በማለት ስለትንሣኤው ሁኔታና ጠላቶቹ የሆኑትን አይሁድንና አጋንንትን ድል እንዳደረጋቸው ዳዊት ተናግሯል። (መዝ. ፸፯÷፷፭) ፍቅር ጽኑዕ ኃያል እንደሆነች እናውቃለን፤ ቢሆንም አንዱ ሌላውን ራሱን ለሞት አሳልፎ እስኪሰጥ ሲወድ አላየንም። እግዚአብሔር ግን ለፍጡሩ ያለው ፍቅር አገብሮት እነሆ ሟች ሥጋ ለበሰ ሞተም "ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሆ እስከ ለሞት" (ወልድን የሰው ፍቅር ከዙፋኑ ስቦ አወረደው እስከ ሞትም አደረሰው) እንዳለ ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም። ሞቶ ግን አልቀረም ድል አድርጎ ተነሳ እንጂ፤ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን አስነሣዋለሁ" ብሎ ነበርና። (ዮሐ. ፪÷፲፱፣ማቴ. ፳÷፲፱)

## ተስፋ ትንሣኤ

አዳም በገነት በተቀመጠ ጊዜ አንድ የተሰጠው ትዕዛዝ ነበር፤ ከዕፀ በለስ እንዳይበላ። ይህንን ጥሶ ቢገኝ የሞት ሞትን እንደሚሞት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል። ቢሆንም የህግ ተገዢ አልሆነምና ያቺን ፍሬ በላ፣ ሞትንም ሞተ፣ ከገነትም ተባረረ። በእንጻረ ገነት በደብር ቅዱስ ሲኖር፤ አንድ ቀን አእዋፍ ለምግብ ካመጡለት የገነት ፍሬ ይዞ ወደገነት መጓዝ ጀመረ። በአንድ አስቸጋሪ ቦታ ላይም ጠላቱ ዲያብሎስ አገኘውና፤ ዛሬስ ገድዬ ላሳርፈው ብሎ በድንጋይ ጉልበቱን መታው። ደሙ ፈሰሰ፣ አጥንቱ ተከሰከሰ። ከፈሰሰው ደሙ በያዘው ፍሬ ለውሶ መስዋዕት አቀረበ። እግዚአብሔርም በእርሱ ደም ሳይሆን ከ፭ ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጁ ተወልዶ፣ ተሰቅሎ፣ ሞቶ አዳም የሞተውን ሞት በአንድ ልጁ ሞት ድል አድርጎ እንደሚያስነሳው፤ ቃል ገባለት። (መቅድመ ወንጌል) ይህችን የትንሣኤ ተስፋ የያዘው አዳም በሲኦል ሆኖ ጌታውን ይጠባበቅ ነበር። አባቶቻችን ነቢያትም ይህንን ተስፋ ያደርጉ ነበር። ለዚህ ነው ክቡር ዳዊት "ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፣ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።"እያለ የዘመረው (መዝ. ፲፭(፲፮)÷፲)

የተነገረው ዘመን ሲፈፀም እነሆ የገባውን ቃል ኪዳን ተግባራዊ ለማድረግ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ሰው ሆነ። "እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ።"(ዘፍ. ፫÷፳፪) እንዳለ አካላዊ ቃልና ሰብዓዊ አካል ተዋሕደው ፍፁም አንድ ሆነ። ዲያብሎስ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ አዳምን እንደ ገደለ፤ እግዚአብሔርም የሰውን ሥጋ ለብሶ ምሥጢርን በምሥጢር ፈትቶ ያድነው ዘንድ ይገባልና በንፅህና ከጠበቃት እመቤታችን ተወለደ በግዕዘ ሕፃናትም (በሕፃናት ጠባይ)አደገ።

## ስቅለተ ዓርብ

ከይሲ ዲያብሎስ ያሳታቸው አዳምና ሔዋን ዓርብ ዕለት በተሰአት ከገነት እንደወጡ፤ በዚህች ዕለትና ሰዓት ወደ ገነት ሊመለሱ ተገባቸው። እነሆ ፈጣሪ ኩሉ ዓለም እነርሱ የብርሃን ልብስ ይለብሱ ዘንድ እርሱ ተራቆተላቸው፤ እነርሱ ይረኩ ዘንድ እርሱ ተጠማላቸው፤ እንደ ወንበዴ በጥፊና በገመድ ተደበደበ። ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙለት እርሱ ዙፋኑን በመስቀል ላይ አደረገ። የብርሃን አክሊል ጌታ የእሾክ አክሊል ደፋ። ከዋክብት ረገፉ፣ ጨረቃም ደም መሰለች፣ ምድርም ተናወጠች፣ ጌታቸው ሲሰቀል መጽናት አልቻሉምና። ጌታ በሥጋው ወደ መቃብር ሲወርድ፤ በነፍሱ ወደ ሲኦል ሄዶ አዳምን ከነወገኖቹ እንደተስፋ ቃሉ ገነትን አወረሳቸው። ስለዚህ ሁኔታ ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ይላል። "ሲኦል ተነዋወጠች፣ መሰረቶቿም እፈርስ እፈርስ አሉ፣ ምድርም ያለጊዜዋ እንዳታልፍ አፀናት፣ ደሙን በምድር ላይ አፈሰሰ፣ ከኀልፈት ጠበቃት በእርሷ ያለውንም ሁሉ ጠበቀ።" (ሃይ. አበ. ዘአት. ፳፯÷፲፫) የዲያብሎስ ጥበብ ከንቱ ሆነ። ሥጋን ተዋሕዶ በመስቀል ላይ ሆኖ "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ" ሲል ቢሰማው ተታለለ፤ እሩቅ ብእሲ (አምላክነት የሌለው) መስሎት ነፍሱን ሊቀራኝ ወደ መስቀሉ ቢቀርብ በእሳት ዛንጃር በነፋስ አውታር ታሰረ መንቀሳቀስም ተሳነው "ከቶ ሥጋን ለብሶ ያሸነፈኝ ይህ ማን ነው?" አለ ሲኦልን ግን ከመበዝበዝ ሊያድናት አልቻለም።

## ትንሣኤው እንዴት ነበር

የጌታችንን ሥጋ ዓርብ በሠርክ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ገንዘውት በአዲስ መቃብር ቀበሩት ንጹሐ ባሕርይ ነውና። አንድም የኤልሳዕ አጥንት ሙት እንዳስነሳ እሱም የጻድቅ ሰው አጽም ነክቶት ተነሳ እንዳይሉ ምክንያት ሲያሳጣቸው። አይሁድ በቅንዓትና በተንኮል ይነሱበት እንጂ፤ የሚናገረውን ነገር ያስተውሉ ነበር። ስለዚህ ከመሞቱ አስቀድሞ እነሳለሁ ማለቱን አስበው፤ ደቀመዛሙርቱ ሰርቀው እንዳይወስዱትና ተነሳ እንዳይሉ በማለት፤ እጅግ በጣም ትልቅ ድንጋይ ገጥመው፣ ማኅተማቸውን አትመው፣ ዘቦቻቸውን አቁመው በከፍተኛ ትጋት አስጠበቁት። ነገር ግን የጌታ ትንሣኤ መቃብር ክፈቱልኝ፣ ድንጋይ ፈንቅሉልኝ፣ መግነዝ ፍቱልኝ የሚያሰኝ አልነበረምና፤ ሳያዩትና ሳይሰሙት እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በአይሁድ ልማድ መሠረት መቃብሩን ሽቱ ሊቀቡ ሴቶች በመጡ ጊዜ፤ የትንሣኤውን ዜና ሊያበስራቸው መልአከ እግዚአብሔር ከሰማይ ወረደ፣ ምድርም ተነዋወጠች፣ ዘቦቹም የሞቱ ያህል ሆኑ ድንጋዩንም ፈንቅሎ "ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ ተነስቷል እንጂ በዚህ የለም በማለት የመቃብሩን ባዶነት አሳያቸው።" (ሉቃ. ፳፬÷፮)

ጌታ የተነሣው በፍፁም ሥጋው ነው የሞተው በሥጋ ነውና። ለመለኮትስ ሞተ ተነሳ አይባልም የእርሱ ባሕርይ አይደለምና(ቄርሎስ) "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ እንዳለ"ለመሆኑ በሥጋ እንደሞተ የተለገረለት ማን ነው? መለኮት ነው። ሥጋ መሞት ባሕርዩ ነውና መለኮትም ሥጋን ስለተዋሃደ በሥጋ ሞተ ተባለ። ሥጋም መለኮትን ስለተዋሃደ ባሕርዩ ያልሆነውን ህያውነት ገንዘብ አደረገ። በመለኮት ህያውነትን እንዳገኘ ተነገረለት። (፩ጴጥ. ፫÷፲፰) እንዲሁም ከትንሣኤው በኋላ በመብላት በመጠጣቱ መከራ በተቀበለበት ሥጋ መነሣቱን አስረድቷል። (ሉቃ. ፳፬÷፴፱)

ትንሣኤውን በሦስት ነገር ገለጠ
፩. ከመያዙ አስቀድሞ እንደሚሞት ነገር ግን በሦስተኛው ቀን እንደሚነሳ ያስ

➔

ተምራቸው ነበር። (ማቴ.፳÷፲፱፣ ማር. ፱÷፱፣ ዮሐ. ፪÷፲፱)

፪. መቃብሩን ከመግነዙ በስተቀር ባዶ ሆኖ አግኝተውታል።(ዮሐ.፳÷፯፣ ማቴ. ፳፰÷፭)

፫. ባለቤቱ ራሱ በተለያየ ቦታ እየተገለጠ ታያቸው ይኸውም

- ለመግደላዊት ማርያም (ዮሐ. ፳÷፲፩)
- ለሉቃስና ቀለዮጳ (ሉቃ. ፳፬÷፲፫)
- በዝግ ቤት ለሐዋርያት (ዮሐ. ፳÷፳፮)
- በደብረ ዘይት ሲያርግ (ሐዋ. ፩)

## የትንሣኤው ምሥጢር

<u>ሥርየተ ኃጢአት</u>:-

ኃጢአት የሰው ልጅ በፈቃዱ ኀትቶ ያመጣው ነገር እንጂ፤ ከባሕርይ የተገኘ አይደለም። አበው "ኀትቶ ያስገቡት ኀትቶ ያስወጣል" እንዲሉ ኀትተን ያመጣነው ኃጢአት ከገነት ኀትቶ አስወጥቶናል። በዘር ውርስ እየተላለፈ ቀንበሩን አክብዶብን ሲኖር፤ ክርስቶስ ያለ ዘርዐ ብዕሲ ተፀንሶ፣ ስለእኛ ኃጢአት እርሱ ሞቶ በትንሣኤው ኃጢአትን ደመሰሰልን። (፩ቆሮ. ፲፭÷፬) ቁጥሩ ከሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት የሆነው እለእስክንድሮስ፤ ሕግ አፍራሽ ጲላጦስ ይዘብትበት ዘንድ፣ በመስቀል ይሰቀል ዘንድ፣ በመቃብር ይቀበር ዘንድ፣ በሦስተኛው ቀን ይነሳ ዘንድ ምን አተጋው? በፍዳ ተይዘን የነበርን እኛን ያድነን ዘንድ ለእኛ ብሎ አይደለምን?" በማለት በአንክሮ ገልፆታል።

<u>ድል በሞት ላይ</u>:-

ለ፭ሺ፭፻ ዘመን ሰልጥኖብን የኖረ ሞት ድል ተነሳ ሞት ሆይ ቸነፈርህ ወዴት አለ? ሲኦል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት አለ? (ሆሴ. ፲፫÷፲፬፣ ፩ኛ ቆሮ.፲፭÷፶፭) ለማለት በቃን። ስለዚህም ሞትን የምንፈራው ሳይሆን ሰማያዊ አክሊልን ለመቀዳጀት የምንናፍቀው ሆነልን። ለዚህም ነው ሰማዕታት ያለፍርሃት ለእምነታቸው የሞቱት (፪ኛ ጢሞ. ፬÷፯)"ሥጋውን ከሙታን ለይቶ በአስነሳ ጊዜ ጌታ የሰውን ጠላት ሞትን ድል የነሳበት ጊዜ ይህ ነው።" (ሃይ. አበ. ዘአርከምስ ፱÷፲፫)

<u>ጣዕመ ሕይወት</u>:-

ምድራዊው ኑሮአችን ጣዕም ያገኘበት ነው። ሞተን በስብሰን እንቀራለን ብለን ተስፋ መቁረጥ ቀረና በሰማያዊው ሕይወታችን በምድር የምንዘጋጅበት ሆነልን። ትንሣኤ ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ ሕይወት በሥጋዊ አምሮትና በአጭር ጊዜ ፍላጎት በታጠረ ነበርና።(፩ኛ ቆሮ. ፲፭÷፵፪)

<u>ትንሣኤ ሙታን</u>:-

ሙታን የማይነሱ ቢሆን ኖሮ የሰው ልጅ ሕይወት ከእንስሳት ባልተለየ ነበር። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኩረ ትንሣኤ ሆነላቸው (፩ቆሮ. ፲፭÷፳) ነቢያት "ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም" (መዝ. ፲፭(፲፮) ፲)እያሉ የፀለዩት የተፈፀመበት ነው።

## ትንሣኤ ሲከበር

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሲል ያደረገውን ሥራ ሁሉ በማሰብ በድምቀት ከምታከብራቸው ዘጠኙ ዓበይት በዓላት መካከል አንዱ ትንሣኤ ነው።

ይህም ሲባል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየዓመቱ የሚሞት የሚነሳ ሆኖ ሳይሆን፤ ያንን የ፭ሺ፭፻ የፍዳና የችግር ዘመን በክቡር ደሙ ፈሳሽነት ተላቀን ከዲያብሎስ ተገዢነት ነፃ የወጣንበት ቀን በመሆኑ ነው።

ነገር ግን ትንሣኤን ስናከብር ልናስተውላቸው የሚገቡትን ነገሮች እንዳሉ ግልፅ ነው። ጌታ ተነሣልን እልል ብለን ወደቤታችን የምንገባ ብቻ ሳይሆን፤ የራሳችንን ሕይወትም የምንቃኝበት ሊሆን ይገባል።

ለእኛ ከገቢረ ኃጢአት ወደገቢረ ጽድቅ መመለስ ትንሣኤ ነው፤ ካለማመን ወደማመን መሸገርም ትንሣኤ ነው፤ ለንስሐ መብቃት ትንሣኤ ነው፤ ሥጋ ወደሙን መቀበልም ትንሣኤ ነው፤ ለእግዚአብሔር ታዛዥ መሆን ትንሣኤ ነው፤ በያዙት እምነት መጽናትም ትንሣኤ ነው። (ሉቃ. ፲፭÷፲፩-፴፪፣ሮሜ. ፲፫÷፲፩፣ራዕ. ፳÷፯፣ሮሜ. ፮÷፭-፲፬) ስለዚህ የትንሣኤው ብርሃን ተካፋዮች ለመሆን ትንሣኤ ልቡና ሊኖረን ያስፈልጋል። "እንግዲያውስ በሥጋ ፈቃዳችን የተመላለስንበት ያለፈው ዘመን ይበቃናልና ከዛሬ ጀምሮ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንነሳ።" /፩ጴጥ.፬÷፩-፬/

በተጨማሪም በዘመናችን እንደምንመለከተው በተለያየ የሥጋ ሥራ ለምሳሌ በዳንስ በጭፈራ፣ በብዙ ድግስና በመሳሰሉት ትንሣኤ ሊከበር አይገባም። የትንሣኤን በዓል ምክንያት ብማድረግም በዕለተ ዓርብ በቅዳሜ ሥዑር የዘፈን መርሐ ግብር ተዘጋጅቷል እየተባለ በክርስትና ስም የሚፈጸመውንም ከመንፈሳውያን የማይጠበቅ የፈቃደ ሥጋን ተግባር ቤተክርስቲያናችን ትቃወማለች። ምክንያቱም እንዲህ የሚያደርጉ ሁሉ ጌታችን ስለ እኛ መከራ ሲቀበል ይደሰቱና ይጨፍሩ ከነበሩት ከሰይጣን ግብር አበሮች ከአይሁድ ያስቆጥረናልና። እንዲህ ብናደርግ በትንሣኤው ትንሣኤያችንን በማፅናት ሳይሆን ይባስ የምንቀበርበትን የኃጢአት ጉድጓድ መማስ ይሆንብናል። ስለዚህ በቤተክርስቲያን በመገኘት ድሆችን በመርዳት፣ በማስቀደስ ሥጋ ወደሙን በመቀበል፣ ቃል እግዚአብሔርን በመስማት በፍፁም መንፈሳዊነት ልናከብር ይገባል።

በዓሉን በዓለ ፍስሐ በዓለ ሰላም ያድርግልን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ተምራቸው ነበር። (ማቴ.፳÷፲፱፤ ማር. ፱÷፱፤ ዮሐ. ፪÷፲፱)

፪. መቃብሩን ከመግነዙ በስተቀር ባዶ ሆኖ አግኝተውታል።(ዮሐ.፳÷፯፤ ማቴ. ፳፰÷፭)

፫. ባለቤቱ ራሱ በተለያየ ቦታ እየተገለጠ ታያቸው ይኸውም

- ለመግደላዊት ማርያም (ዮሐ. ፳÷፲፩)
- ለሉቃስና ቀለዮጳ (ሉቃ. ፳፬÷፲፫)
- በዝግ ቤት ለሐዋርያት (ዮሐ. ፳÷፳፮)
- በደብረ ዘይት ሲያርግ (ሐዋ. ፩)

## የትንሣኤው ምሥጢር

ሥርየተ ኃጢአት:-

ኃጢአት የሰው ልጅ በፈቃዱ ኀትቶ ያመጣው ነገር እንጂ፤ ከባሕርይ የተገኘ አይደለም። አበው "ኀትቶ ያስገቡት ኀትቶ ያስወጣል" እንዲሉ ኀትተን ያመጣነው ኃጢአት ከገነት ኀትቶ አስወጥቶናል። በዘር ውርስ እየተላለፈ ቀንበሩን አክብዶብን ሲኖር፤ ክርስቶስ ያለ ዘርዐ ብዕሲ ተፀንሶ፣ ስለእኛ ኃጢአት እርሱ ሞቶ በትንሣኤው ኃጢአትን ደመሰሰልን። (፩ቆሮ. ፲፭÷፬) ቁጥሩ ከሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት የሆነው እለእስክንድሮስ፤ ሕግ አፍራሽ ጲላጦስ ይዘብትበት ዘንድ፣ በመስቀል ይሰቀል ዘንድ፣ በመቃብር ይቀበር ዘንድ፣ በሦስተኛው ቀን ይነሳ ዘንድ ምን አተጋው? በፍዳ ተይዘን የነበርን እኛን ያድነን ዘንድ ለእኛ ብሎ አይደለምን?" በማለት በአንክሮ ገልፆታል።

ድል በሞት ላይ:-

ለ፭ሺ፭፻ ዘመን ሰልጥኖብን የኖረ ሞት ድል ተነሳ ሞት ሆይ ቸነፈርህ ወዴት አለ? ሲኦል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት አለ? (ሆሴ. ፲፫÷፲፬፤ ፩ኛ ቆሮ.፲፭÷፶፱) ለማለት በቃን። ስለዚህም ሞትን የምንፈራው ሳይሆን ሰማያዊ አክሊልን ለመቀዳጀት የምንናፍቀው ሆኖልን። ለዚህም ነው ሰማዕታት ያለፍርሃት ለእምነታቸው የሞቱት (፪ኛ ጢሞ. ፬÷፮)"ሥጋውን ከሙታን ለይቶ በአስነሳ ጊዜ ጌታ የሰውን ጠላት ሞትን ድል የነሳበት ጊዜ ይህ ነው።" (ሃይ. አበ. ዘአርክዎስ ፱÷፲፫)

ጣዕመ ሕይወት:-

ምድራዊው ኑሮአችን ጣዕም ያገኘበት ነው። ሞተን በስብሰን እንቀራለን ብለን ተስፋ መቁረጥ ቀረና በሰማያዊው ሕይወታችን በምድር የምንዘጋጅበት ሆነልን። ትንሣኤ ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ ሕይወት በሥጋዊ አምሮትና በአጭር ጊዜ ፍላጎት በታጠረ ነበርና።(፩ኛ ቆሮ. ፲፭÷፴፪)

ትንሣኤ ሙታን:-

ሙታን የማይነሱ ቢሆን ኖሮ የሰው ልጅ ሕይወት ከእንስሳት ባልተለየ ነበር። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኩረ ትንሣኤ ሆኗቸው (፩ቆሮ. ፲፭÷፳) ነቢያት "ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተውውም" (መዝ. ፲፭(፲፮)፲)እያሉ የፀለዩት የተፈፀመበት ነው።

## ትንሣኤ ሲከበር

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሲል ያደረገውን ሥራ ሁሉ በማሰብ በድምቀት ከምታከብራቸው ዘጠኙ ዓበይት በዓላት መካከል አንዱ ትንሣኤ ነው።

ይህም ሲባል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየዓመቱ የሚሞት የሚነሳ ሆኖ ሳይሆን፤ ያንን የ፭ሺ፭፻ የፍዳና የችግር ዘመን በክቡር ደሙ ፈሳሽነት ተላቀን ከዲያብሎስ ተገዢነት ነፃ የወጣንበት ቀን በመሆኑ ነው።

ነገር ግን ትንሣኤን ስናከብር ልናስተውላቸው የሚገቡትን ነገሮች እንዳሉ ግልፅ ነው። ጌታ ተነሣልን እልል ብለን ወደቤታችን የምንገባ ብቻ ሳይሆን፤ የራሳችንን ሕይወትም የምንቃኝበት ሊሆን ይገባል።

ለእኛ ከገቢረ ኃጢአት ወደገቢረ ጽድቅ መመለስ ትንሣኤ ነው፤ ካለማመን ወደማመን መሻገርም ትንሣኤ ነው፤ ለንስሐ መብቃት ትንሣኤ ነው፤ ሥጋ ወደሙን መቀበልም ትንሣኤ ነው፤ ለእግዚአብሔር ታዛዥ መሆን ትንሣኤ ነው፤ በያዙት እምነት መጽናትም ትንሣኤ ነው። (ሉቃ. ፲፭÷፲፩-፴፪፤ሮሜ. ፲፫÷፲፩፤ራዕ. ፳÷፮፤ሮሜ. ፮÷፭-፲፬) ስለዚህ የትንሣኤው ብርሃን ተካፋዮች ለመሆን ትንሣኤ ልቡና ሊኖረን ያስፈልጋል። "እንግዲያውስ በሥጋ ፈቃዳችን የተመላለስንበት ያለፈው ዘመን ይበቃናልና ከዛሬ ጀምሮ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንነሳ።" /፩ጴጥ.፬÷፩-፬/

በተጨማሪም በዘመናችን እንደምንመለከተው በተለያየ የሥጋ ሥራ ለምሳሌ በዳንስ በጭፈራ፣ በብዙ ድግስና በመሳሰሉት ትንሣኤ ሊከበር አይገባም። የትንሣኤን በዓል ምክንያት ብማድረግም በዕለተ ዓርብ በቅዳሜ ሥዑር የዘፈን መርሐ ግብር ተዘጋጅቷል እየተባለ በክርስትና ስም የሚፈጸመውንም ከመንፈሳውያን የማይጠበቅ የፈቃደ ሥጋን ተግባር ቤተክርስቲያናችን ትቃወማለች። ምክንያቱም እንዲህ የሚያደርጉ ሁሉ ጌታችን ስለ እኛ መከራ ሲቀበል ይደሰቱና ይጨፍሩ ከነበሩት ከሰይጣን ግብር አበሮች ከአይሁድ ያስቆጥረናልና። እንዲህ ብናደርግ በትንሣኤው ትንሣኤያችንን በማፅናት ሳይሆን ይባስ የምንቀበርበትን የኃጢአት ጉድጓድ መማስ ይሆንብናል። ስለዚህ በቤተክርስቲያን በመገኘት ድሆችን በመርዳት፣ በማስቀደስ ሥጋ ወደሙን በመቀበል፣ ቃል እግዚአብሔርን በመስማት በፍፁም መንፈሳዊነት ልናከብር ይገባል።

በዓሉን በዓለ ፍስሐ በዓለ ሰላም ያድርግልን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር